# ወቅ ያ ቢ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

Amara Survival For Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም፳፯ | ቀን: መስከረም ፯ | በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## የሕዝቡን ትኩረት የሳቡ ወቅታዊ ጉዳዮች!!

እንኳን ዘንድሮ የለዉጥ አየር እየነፈሰ ነዉ በሚባልበት አዲስ ዓመት ይቅርና በነዚያ ከፉ ፳፯ የትህነግ/ኢሕአዴግ መድሎአዊና ጭካኔ በተሞላበት ፋሽሽታዊ መስተዳደር ዓመታት ጊዜም እንኳ ቢሆን ሕዝባችን አሮጌዉ ዓመት አልፎ አዲሱ ሲተካ "ከዘመን ዘመን መሸጋሩን ተስፋ ብሎት" ሁሌም ፈጣሪዉን አመስግኖ በመጻዊዉ አዲስ ዓመት ልቡ ተስፋን አጭሮ በሆደ ሰፊነት አሮገዉን ይሸኘዋል እንጅ እ/ብሔርን ና ዉረድ ብሎ አያማርርም።

አዎ! እርግጥ ነዉ የግፉ ጽዋ መልቶ መፍሰሱ የግድ ሲሆን ግን ቄሮዎችና ዘርማዎች በሰላማዊ አመጽ አምርረዉ ሲገፉ እነ ሞት አይፈሬ ፋኖዎች/የጎበዝ አለቆች ደግሞ እስከ አንገቱ ከታጠቀዉ የአጋዚ ጦር ጋር እስከ ቀራኒዮ ፊት ለፊት መጋፈጣቸዉ የተገነዘቡ "የቲም ለማ" የለዉጥ አራማጆችና መሪዎች ደግሞ ጥረታቸዉና ምኞታቸዉ ሰምሮና ለሕዝብ ስሜትና ፍላጎት ቅድሚያ መስጠት በመቻላቸዉ እነሆ የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ከፍተኛ የአመራር አካላት እንደሌሎች ድርጅቶች ሁሉ በአዲሱ ዓመት ዋዘሚያ ወደ ሀገር ቤት ገብቶ በሕዝባችን ዉስጥ ሆኖ በሰላማዊ መንገድ ታግሎ ለማታገል ትግሉን ጀምረዉታል።

እርግጥ ነዉ የተገኘዉን መልካም የለዉጥ መንፈስ ይበልጥ ወደ ተሻለ ደረጃ ለመግፋት በሕዝባችን መካከል መገኘታችን ደስ ቢለንምና የጠ/ሚ ዶ/ር ዐብይ አሕመድ ተፎካካሪ ድርጅቶች ወደ ሀገር ቤት ገብተዉ በሰላማዊ መንግድ እንዲንቀሳቀሱ ማበረታታቸዉ ጥሩ ርምጃ ቢሆንም ቅሉ በዚያም ልክ ግን ላለፉት ፳፯ ዓመታት ከፖለቲካዉ መድረክ ሆን ተብሎ ተገልሎና የጥቃት ሰለባ ሆኖ የቆየዉ የዐማራ ነገድ ሕዝባችን ዛሬም ድረስ አንጃበበት ያለዉ አስፈሪ የጦርነት አደጋ ስናይ ግን "ኧረ በሕግ አምላክ" መፈናቀሉ፣ መዋከቡና መገደሉ ይቁም ለማለት ተገደናል።

ከጎንደር ክ/ሀገር በወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምትና አካባቢዉ እንዲሁም ከወሎ ክ/ሀገር በእንዳ መሃሪ፣ ራያ፣ ወፍላና አላማጣ ዛሬ የሕጎች ሁሉ ሕግ ነዉ ከሚባለዉ የወያኔና አኮግ ሕገመንግሥት በፊት በትህነግ ሕገወጥ መንገድ በኃይል በወረራ የተያዙ በመሆናቸዉ ምክንያት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ በፊቱ ሕጋዊ ባለቤታቸዉ የዐማራ አስተዳደር እንዲመለሱ እየጠየቅን ሳለና የዐማራ ማንነት ጥያቄ ከታፈነበት በአደባባይ ፈንቅሎ ወጦ "የምልአተ ሕዝቡ ወሳኝ አጀንዳ" ሆኖ በመቅረቡ እልባት እንዲያገኝ ብዙ ጥረት እየተደረገ እያለ ይባስ ብሎ በዚህ የለዉጥ መልካም ጅማሮ ወቅት ሳይቀር ከላይ በተጠቀሱት መሬቶችና አካባቢዎች በታሪክ ከሚታወቀዉ ትግራይ ክ/ሀገር (ትግራይ ጠ/ግዛት) በመጡ ከባድና የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ታጣቂዎችና አዳዲስ ሰፋሪዎች ትምህርት ቤቶችና የግለሰብ ቤቶች ሳይቀር መሞላታቸዉ መታየቱ እጅግ በጣም አስደንጋጭ ድርጊት መሆኑ ነዉ።

በዚህ የለዉጥ ወቅትና የዐማራ ማንነት ጥያቄ እጅግ በጣም ጎልቶ በወጣበትና ሁነኛ እልባት ማግኘት የግድ ነዉ በሚባልበት ወቅት ይባስ ብሎ ታጣቂ ኃይልና አዳዲስ ሰፋሪዎችን ከትግራይ እያመጡ በጣምራ ማስማራት በሰላማዊ የዐማራ ነገድ ተወላጆችና እርስቶች ላይ አንጃበ ያለዉን አስፈሪ አደጋ በግልጽ ያሳያል። ይህንም አስፈሪ ሁኔታ አስመልክቶ በመከላከያ ሚኒስትር የሰሜን እዝ አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ጌታቸዉ ጉዲናም "በአጎራባች ክልሎች ወሰን አካባቢ የታጠቀ ኃይል የማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ይታይሉ" በማለት በአደባባይ ከመናገራቸዉ ባሻገር የፌዴራልና የአጎራባች ክልል መስተዳድሮች የጉዳዮን አሳሳቢነት በመገንዘብ በአስቸኳይ መፍትሔ እንዲሹ በአጽንዖት በአደባባይ አሳስበዋል። ይህም በቀጥታና በግላጭ የሚያሳየዉ ትህነግ ወደ እዉነተኛዉ የመፍትሔ ሃሳብ ለመምጣትና በኃይል የወረራቸዉን አካባቢዎች ለሕጋዊ ባለቤቱ ለመመለስ መዘጋጀቱን ሳይሆን የሚያሳየዉ ትህነግ በወረራ አስቀድሞ የያዛቸዉን የጎንደርና ወሎ ክ/ሀገር የዐማራ ግዛቶች/እርስቶች አሁንም በኃይልና በኃይል ብቻ ወረራዉን አጠናክሮ ለመቀጠል ያለዉን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ከመሆኑ ባሻገር አሁንም ከለላና አጋዥ የሌለዉን ሰላማዊ የዐማራ ነገድ ወገናችንን ለበለጠ እመቃ፣ ስቃና ግድያ ለመዳረግ እየሰራ መሆኑን በሚገባ ያሳያል።

ከጎንደርና ወሎ ክ/ሀገሮች በኃይል በተወረሩ ግዛቶች ዉስጥ የዐማራ ወጣቶችና የታሪክ አዋቂዎች እንደዋዛ ይገደላሉ፣ ይታፈናሉ እንዲሁም ይደበደባሉ፣ ከባድማቸዉ እየተፈናቀሉ በተለያዩ ጊዜአቶች ከትግራይ በመጡ አዳዲስ ሰፋሪዎች ተገፍተዉ ይጣላሉ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በተመሳሳይ ሁኔታ የጎጃም ክ/ሀገር መተከል አዉራጃ ዉስጥ በነ አዜብ ጎላና ዘመዳሞች የጥጥ ማዳመጫ ሰራተኝነት ስም የተመለመሉት በትህነግ አስልጣኞች ወታደራዊ ስልጠናዉን ጨርሰዉ ሳይዉል ሳያድር የበፊቱን ጥቃት አጠናክረዉ የዐማራ ነገድ ተወላጆች ላይ ከአባቶቻቸዉ እርስት የማፈናቀሉና በግድያ የማሳደዱ ሁኔታ ዛሬም ተጠናክሮ ቀጠለ እንጅ ቁጥጥር ሲደረግባቸዉ አልታየም።

በመሆኑንም በቅርቡ በጅጅጋና አካባቢዉ የደረሰዉ ተመሳሳይ አሰቃቂ አደጋ አይደርስም ለማለት ከቶ አያስደፍርምና ጉዳዮ የሚመለከታቸዉ የተለያዩ የመንግሥት አካላትና ራሱ ብአዴን ጭምር እንዲሁም አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጊቱን ሊያወግዘዉና አካባቢዉ ከትግራይ ወታደሮች ወራሪ ኃይል ነፃ እንዲሆንና ቋፍ ላይ ያለዉ ችግር ሁነኛ እልባት እስኪያገኝ ድረስ ቢያንስ ቢያንስ ሁሉም አካባቢዎች በገለልተና ነፃ ኃይል/አካሎች መጠበቅ ይኖርባቸዋል ብሎ ዐኅኢአድ በጽሞና ያሳስባል/ያሳስባል።

የዚህ ጽሁፍ አስፈላጊነት ዋና ምክንያትም ይህን ከላይ በአጭሩ ለማንሳት የተሞከረዉ አሳሳቢ ጉዳይ በአቸኳይ ትኩረት አግኝቶ ቢያንስ ቢያንስ ችግሩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ወገኖች ጋር በዉይይት ሁነኛ መፍትሔ እስኪያገኝ ጊዜ ድረስ በወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምትና አካባቢዉ፣ እንዲሁም በወሎ እንዳመሃሪ፣ ወፍላ፣ ራያና አላማጣ የሚኖረዉ ወገናችን ከትህነግ ወረራ ነፃ ሆኖ መንግሥታዊ ጥበቃና ከለላ የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ እዲፈጠር ጉዳይ የሚመለከታቸዉ ሁሉ አፋጣኝ ርምጃ እንዲወስዱ ለማሳሰብ ሲሆን እግረ መንገዳችን ሰሞኑን እየታዩና እያወዛገቡ ባሉ ጉዳዮች የመዲናችን ጉዳዮ ላይ ማለትም የእ/ር ስመኘዉ ግድያ ከፍትህ አኳያ ሲታይና ከሜቴክ ጋር በተየያዘ እየተነሱ ያለዉ ምዝበራዎች፣ ስለ አዲስ አበባ ወጣቶች "ጎሮ ወሸባዬ" አቀባበልና ከኦነግ መሪ አቶ ዳዉድ ኢብሳ ጋር በተያያዘ የተነሱ ዉዝግቦችን እንደ ድርጅት መዳሰሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷልና እንደሚከተለዉ በጣም ባጭር የዐኅኢአድ ምልከታ ቀርቧል።

የኢ/ር ስመኘዉ በቀለን ግድያ አስመልክቶ የወጣዉ የመንግሥት ዘገባ/ሪፓርት የብዙዉን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሕሊና የገዛ ሆኖ አለመገኘቱን ሁሉም የተገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ። ለዚህም ከመረጃ አሰባሰብ ሂደት ጀምሮ ብዙ የመከራከሪያ ምክንያቶች በታዛቢዎች ቀርበዋል። በዚህ ረገድ ዐኅኢአድ ለአንድ ዜጋና የሀገር ተቆርቋሪ ድርጅት የሚኖረዉ እይታ ከፍትህና ርዕትህ (ሕግ) አኳያም መታየት ያለበት ጉዳይ በመሆኑ በዚህ በለዉጥ የታሪክ ምዕራፍ ላለ አምራር/መንግሥት በፊት የነበረዉን መንግሥታዊ መዋቅር እንዳለ ተጠቅሞ ታማኒ የሆነ የማጣራት ሥራ ይሰራል ብሎ ከመገመት ይልቅ ከመጀመሪያዉ ጀምሮ የማጣራቱ ሂደት የገለልተኛ ሕጋዊ አካል ቢይዘዉ ወይም ካለዉ መንግሥታዊ መዋቅር ጋር ገለልተኛ አካል ጎን ለጎን አብሮ የሚሰራበት ሆኔታ ቢኖር ኖር እዉነቱን ለማጣራትና ዉጤቱን ቅቡል ለማድረግ የተሻለ አሳማኝ ሁኔታ ይፈጥር ነበር ብሎ ያምናል። በመሆኑም አሁንም ቢሆን ይህ ዕድል ክፍት ሆኖ ጉዳዩ በሚገባ እንዲጣራና በተለይ ደግሞ በሜቴክ ዙርያ ገና ከጅምሩ ጀምሮ በተለያዩ አካላት እየተጠቆሙት ያሉት የብክነትና ሙሰኝነት ጉዳዮች አሁንም ያለምንም ቅድመሁኔታ በገለልተኛ አካል መያዝ እንዳለባቸዉ ዐኅኢአድ በጽሞና ያምናል።

ሌላዉ የኦነግ አመራር አቶ ዳዉድ ኢብሳ ወደ ሀገር ቤት መምጣታቸዉን ምክንያት በማድረግ ከነበረዉ የአቀባበል መርሃግብር ጋር በተያዘ በአዲስ አበባና አካባቢዉ የተነሳዉ ግርግርና ግጭት እጅግ በጣም አሳዛኝ መሆኑን ዐኀኢአድ እየገለፀ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ሁኔታዎችን ቀረብ ብሎ ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል። በተለይ ደግሞ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጉዳዮ የሚመለከታቸዉ የመንግሥት አካሎችና የግንቦት ሰባት አመራሮች የሰጡትን መግልጫ በትቂቱ መዳሰብ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል።

ከዚያ በፊት ግን እንደ ግንዛቤ መያዝ ያለበትን እናሳይ!! ያም አዲስ አበባ የአገራችን መዲና ከመሆን አልፋ ኢትዮጵያ በአባቶቻችን የአርበኝነት ታሪክና ተጋድሎ ለጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲልና ተምሳሌት ተደርጋ ስለተወሰደች (አዲስ አበባ) የአፍሪካ አኅጉር ዋና ከተማም ጭምር ነች ማለት ይቻላል። ይህ ታላቅ ክብር ለኢትዮጵያ የተሰጠዉ እጣ በመጣጣል የተገኘ ሳይሆን የሁላችንም የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አባቶቻችን በከፈሉት አኩሪ ታሪካቸዉ/ችን ነዉ። ከዚህ አኳያ ዐኀኢአድ ለአዲስ አበባ የሚመጥን ዘመናዊ አስተሳስብ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ ሊኖር ይገባል ብሎ በጽኑ ያምናል። ዘመናዊ ሲባልም የአዲስ አበባን ታሪካዊነት፣ ታላቅነትና የዲፕሎማት ከተማ መሆናን ግምት ዉስጥ ባስገባና ለሁሉም ኢትዮጵያዉያን እኩል ዋና ከተማ መሆኗን መሰረት ያደረገ ለማለት ነዉ። እርግጥ ነዉ ትህነግ ለመሰሪ ዓላማዉ ማስፈጸሚያና ለከፋፍሎ መግዛት እንዲመቸዉ ኢትዮጵያን በዐማራ ነገድ ብቻ እየሳለ ብዙ እንደሰራበት ብናዉቅም ዐኀኢአድ ግን ኢትዮጵያ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ ታሪካዊ ቅርኝት ዉጥት ነች ብሎ ነዉ የሚያምነዉ!!

ስለዚህ አዲስ አበባ ሁሉንም በሰላምና በመከባበር ላይ በተመሰረተ የፖለቲካ ብሂልና አመራር ላይ የመቀበልና የማስተናገድ ኃላፊነት ሊኖራት ይገባል ለማለት ነዉ። ለዚህ ደግሞ ራሱን ለመመራት ዛሬም ድረስ ዕድል አይሰጠዉ እንጅ ተቻችሎና ተከባብሮ ለመኖር የአዲስ አበባ ነዋሪ ለአፍታም እንኳ አይታማም። ለዚህም ለዘመናት ተቻችሎ የኖረበትን ያን ረጅሙን ታሪክ ትተን ትላንት በሰኔ ፲፮ ቀን ፳፻፲ በራሱ አነሳሽነት ለጠ/ር ዶ/ር አብይ ድጋፉን ለማሳየት ብሎ በነቂስ የወጣዉ የአዲስ አበባ ነዋሪ የተለያዩ ድርጅት ዓርማዎችን፣ ምልክቶችንና ታሪካዊ የኢትዮጵያን ሰንደዓላም ጭምር ይዞ በአደባባይ ወጧል። በዚያ ሂደት ዉስጥ የቀን ጅቦች ከሚባሉት የጥቃት ሙከራ ከማድረግ በስተቀር ከሕዝቡ ወገን አንዲትም ኮሽታ አልነበረችም።

ታዲያ እዉነታዉ ይህ ሆኖ ሳለ የሰሞኑን የአዲስ አበባ ወጣቶች ለግጭት የዳረገዉ ማነዉ? ለምን ወደ ግጭት ሄዱ? ማን, , , የማንን መብት ተጋፋ? ተንኳሹስ ማን ነበር? የሚሉትን ጉዳዮች በጽሞና ማየትና ሚዛናዊ ሕሊናዊ ፍርድ መስጠት ተገቢ ሆኖ ሳለ የመንግሥትን የዜና አዉታር በመጠቀም ከግራ ቀኝ የቀረበዉ አስተያየት ሁሉ ጥቃቱንና ትችቱን ወደ አንድ አቅጣጫ ያዞረ በሚመል መልኩ ቀርቧል። አንዳንዶች በስሜትና በጥላቻ ፈረስ እንደለመዱት ዛሬም እየጋለቡ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት ያሉበትን የኢትዮጵያን ሰንደቃአላማ ልክ የዐማራ የግሉ ሰንደቅዓላማ አድርገዉ የፈጠራ ትርክት እያቀረቡ ወጣቱ ትዉልድ የአባቶችን አኩሪ ታሪክ አጠልሽተዉና አሳንሰዉ ያቀርቡነታል። ይህም ቀርቶ የግለሰቦችን ቤት ሳይቀር በጥላቻ ተነሳስቶ እያቀለመ ያለዉ ተንኳሹ ተቀምጦ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ በያዘዉ ላይ ጣታቸዉን ቀሰሩ። በዚህ ረገድ የግንቦት ከፍተኛ አመራር አቶ ኤፍሬምና ዶር ብርሃኑ ሳይቀር እዉነትን ገለልተኛ ሁኖ በጽሞና ከማጣራትና ዉጥረቱን ለማርገብ የተሰጣቸዉን የመንግሥት የብዙሃን መገናኛ ዕድል በሚዛናዊነት ከመጠቀም ይልቅ ልክ እንደ በፊቱ ሁሉ አሁንም ወደ አንድ ወገን ወገንተኛ ሁነዉ በመቅረብ አቋማቸዉን ግልጽ አደረጉ። ለዚህም አቶ ኤፍሬም ታሪካዊዉን የኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ በድፍረት “ሁሉም ሕዝብ አይቀበለዉም” ብሎ ከማወጁ ባቻገር አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩን ሰንደቅዓላማ በያዙት ላይ ብዙ … ብዙ ቅስቀሳና ጥፋተኛች እንደሆኑ አደርጎ ቀሰቀሰ።

እርግጥ ነዉ የአቶ ኤፍሬም ፀረ-ዐማራነት አቋም ከበፊት ጀምሮ የቆየና ሁሉም የሚያዉቀዉ ለመሆኑ “አዚ ደርሶ መልስ” በሚል በተከታታይ ያወጣቸዉንና በተለያዩ መድረኮች ላይ የገፋቸዉን ፀረ-ዐማራ መፀፃፎቹን አምብቦ መረዳት በቂ ነዉ። ችግሩ የአቶ ኤፍሬም ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የግንቦት ሰባት መሪም በአንድ የምርጫ ጣቢያ(ያዉም በመዐሕድ/መኢአድ መዋቅር ላይ ተንጠላጥሎ) ስለተመረጠ ብቻ እንዲያዉ ደርሶ በአዲስ አበባ ሕዝብ/ነዋሪ የተመረጠ ይመስል ግጭቱን ከማረጋጋት ይልቅ ይበልጥ ሰበብ ሆኖ መቅረቡ ልክ እንደ አቶ ኤፍሬም በተመሳሳይ መልኩ ራሱን ከፍተኛ ትዝብት ዉስጥ መክተቱ ሌላዉ ጉዳይ ነዉ። ያዉም ሳምንት ሳይሞላ!!

ግንቦት ሰባት አንዷት ጥይት ሳያጮህ ዐማራን ሆን ብሎ ለማሳሰርና ለማስገደል ለትህነግ መሳሪያና ሕጋዊ ምክንያትና ሽፋን ስጭ ሆኖ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ማገልገሉ እየታወቀ አሁን ደግሞ የዐማራዉ ገበሬ ከብቱን ሸጦ ለልጆቹ መጠበቂያ ብሎ የገዛዉን መሳሪያ በሴራና ሸፍጥ ለማስፈታት እያደረገ ያለዉ ሌላዉ የወቅቱ አሳሳቢ ጉዳይ ነዉ። ይህ ወደፊት የምንመለስበት ስለሆነ አሁን እንሄድበት!!

ሌላዉ ከኦነግ አመራር ከአቶ ዳዉድ ኢብሳ አቀባበል ጋር ተያይዞ የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ በአቶ ታከለ ኡማ የቀረበዉ ንግግር እጅግ በጣም አስደንጋጭና ሙሉ በሙሉ ወገንተኛ ከመሆኑ ባሻገር ንግግሩ ሁሉንም የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን ደጎንነትና ሰላም መጠበቅን ግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ የተደረገ "የእንኳን ደኅና መጣህ/መጣችሁ" ዓይነት ንግግር ሳሆን የአንድ አክራሪና ጥንፈኛ ቡድን ስብሰባ ላይ ዋና ተናጋሪ በሚያስመስል መልኩ መቅረባቸዉ በጣም አስደጋጭ ነበር። በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኃላፊዎች በኩልም የቀረበዉም ጋዜጣዊ መግለጫም ያዉ ሙሉ በሙሉ ወገንተኝነት የተጠናወተዉ መሆኑ በግልጽ ታይቷል።

ይህ ዓይነቱ አካሄድ እጅግ በጣም ብዙዉን የኅበረተሰብ ክፍል ያሳዘነ ከመሆኑ ባሻገር ለተጀመረዉ ለዉጥም የኅበረተሰቡን መልካም እያታና ድጋፍ የሚከፋፍል ከመሆኑ ሻገር ይህን ንግግር ተከትሎ በቡራዩና በተለያዩ የአዲስ አበባ ዙርያዎች ለተነሳዉ አደጋ ቤንዚልና ክብሪት የማቀበል ዓይነት ሆኖ ማገልገሉ መታወቅ አለበት። በአጠቃላይ አሁን እየሆነ ያለዉ በብዙ መስዕዋትነት የተገኘዉን የለዉጥ መልካም ጅምር በሰከነና በተረጋጋ መንገድ ወደ ተሻለና ሁሉን ሊያሳትፍ ወደሚቻልበት የተረጋጋ መድረክና አዲስ ምዕራፍ ከፋች አካሄድ እየተሄደ ሳይሆን ቀደም ብሎ በተናጠል በትህነግና ኦነግ የተጀመረዉን አግላይ ሕገመንግሥት ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረግ የፉክክር ሩጫ እስከሚመስል ድረስ የሚሰራ ድርጊት አስመስሎታል።

በዚህ ዓይነቱ አግላይ አካሄድ ደግሞ የትኛዉንም የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የማያደርግ ከመሆኑ ባሻገር የአዲስ አበባ ወጣቶችና አጠቃላይ የከተማዉ ነዋሪዎች በዚያች ክፉ ፈታኝ ወቅት አንዷት ጥይት ላላጮሆ ሁሉ በስሜት እየተነሱ "ጉሮ ወሸባ" ብሎ በስሜትና በግርግር ከመነዳት ይልቅ ለራስ አደብ ገዝቶ አዲስ አበባ በራሷ ነዋሪዎች ቀጥተኛ ተመራጮች የምትመራበትን ሕጋዊ መንግድ መጠየቅ የግድ ነዉ!! በአጠቃላይ የአዲስ አበባ ነዋሪ ለድጋፍና ተቃዉሞ ሰልፍ ከመዉጣት አልፎ የራሱን ተመራጮች ራሱ በቀጥታ መርጦ የመተዳደር ሕጋዊና ተፈጥሮአዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶ ነዉና ቆም ብሎ ያስብ፣ የራሱንም ሕጋዊ ጥያቄ ያቅርብ!! በምስለኔ መመራት፣ በስሜትና በጅምላ መነዳቱ ይብቃ!!

**የዐማራ ኅልዉና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነዉ!!**